# ወያኔ ዘረኛና ፋሽስት፣ ፀረ_ኢትዮጵያና ሕዝቧ ነው
# ልጆችህን አርዶ ሳጨርስ
# በሕዝብ አመጽ በአስቸካይ መወገድ አለበት

ከቀመሩ ደሳለኝ

ወያኔ/ ሕወሓት በትግራይ የበላይነት መሰረተ አሳብ ተመስርቶ ጎጠኝነትንና ፀረ_ ኢትዮጵያ አጀንዳ ይዞ የመጣ በዴሞክራሲ ድባብ ሥር ፍሽዝምን ማካሄዱ ገና የሥልጣን ሎተሪ ሳይደርሰው በፊት በኢትዮጵያ በተለይም በአማራው ላይ አነጣጥሮ የነበረው የጥላቻ ጦር እነሆ ዛሬ በመላ አገሪቱ ውስጥ እየተስተገበረ እያየን ነው ።ወያኔ/ኢህአድግ በጫካ እያለ ፀረ_ አማራ፣ ፀረ_ ኢትዮጵያና ፀረ_ አንድነት፣ ፀረ_ ኅብረተሰብ ፀረ_ሃይማኖት እንደሆነ የጻፋቸው ጹሁፎች እጅግ በርካታና በተግባርም እየፈጸማቸው ይገኛል።

ገዥዎች ሕዝብን በመሳሪያ ኃይል ዝም ማስኘት ዘላለማዊ የሚያደርጋቸው ይመስላቸዋል። በኃይልና በግደታ አፍኖ በመያዝ፣ በማሰርና በማፈን፣ በስውር መግደል፣ በማሳደድና በማፈናቀል ሕዝብን አስወጥቶና አባሮ ሕዝብ ይደግፈናል፣ ሕዝብም ደግፎታል ሲባል ተሰምቷል።ዛሬ በዓለም ሕዝባችን ተሰዶ መከራ የሚቀበለው የወያኔ ሥራ ነው።ወያኔ ዴሞክራት ነኝ ቢለንም ዴሞክራሲን ያዘንባል ተብሎ አልተጠበቀም የሚጠበቅም አይደለም። ወያኔ ተፈጥሮው ዘረኛ፣ ባህሪው ፋሽስት ነውና። ኢትዮጵያን አይወክልምና።የጊዜ ጉዳይ ሆኖ ነው እንጂ እንዲህ እንደ አሁኑ ማንነቱ እንደሚጋለጥ ይታወቅ ነበር።

የትግል መጀመሪያው ጠላትን ማወቅና መለየት ከሆነ ተከታዪ የትግሉን ስልት መቀየስና ማቀነባበር ይሆናል።ወያኔዎች ገና በጫካ እያሉ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነትንና ሰንደቅ ዓላማችንን በጠላትነት ፈርጀውታል። በፀረ_ ኢትዮጵያም ለመንቀሳቀስ ወስኖ ታክቲኮችን ነድፋል።ይህንኑም ዛሬ በመፈጸም ላይ ይገኛሉ።በአገር ወዳዱ ኢትዮጵያዊያን የወያኔ አገር ጠልነት ታውቋል ከጥቂት አድርባይ፣ ሆዳም አገር ሻጭ፣ ግብዞችና ባንዳዎች በስተቀር።

ወያኔዎች በእየአረቡ ደጃፍ እየተዘዋወሩ በልመና ከረጢታቸው በአገኙት ርዳታ የጦር መሳሪያ ገዝተውና በኢትዮጵያ ጠላቶች እየተረዱ አገርና ሕዝብን በመውጋት ለቤተ_ መንሥግት የበቁት ሕወሓትና ሻቢያ ማንነታቸው ዛሬ አገር ያወቀው ፀሐይ ያሞቀው ሆኖል።በእብሪት የተወጠረው ወያኔ/ህውሃት ወትሮም ሰላም የሚለው የውሸት ልፈፋው ከእባብ እንቁላል እርግብ እንደ መጠበቅ ነበር።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ፣ ወያኔ፣ ሻቢያ በወራሪው የጣሊያን ኮሎኒያል ቅኝ ገዥ ዱካን በተከተሉበት አገርን ለመበታተን የሕዝብ አንድነት፣ትስስርና ጥንካሬን ለማናጋት ያላደረጉት አልነበረም። ወያኔ ሥልጣን በያዘ ማግስት ነበር ኢትዮጵያን ለማጥፋት የጦርነት አዋጁን ያሰማው።ከኃይል በመነጨ ሥልጣኑ የወያኔ አገዛዝ እራሱ ወንጅሎ እራሱ ፈራጅ በመሆን በመላ ኢትዮጵያ የወያኔ ሹማምቶች በተገኙበት ሁሉ የኢህአድግ አውታሮች በሚዳረሱበት ስፍራ የአማራውን ሕዝብ ነፍጠኛ በሚል ቅጽል አጅበው ትምክተኞች ዲሞክራሲያችሁን ሊነጥቋችሁ ነውና ምን ትጠብቃላችሁ አትዋጓቸውም ውይ እያሉ ጦርነት ያወጁ እነሱ ነበሩ።በዚህ ሁኔታ ዘለቅ ሲል በአማራው ሕዝብ ላይ ያደረሰው ግፍ፣ስቃይና መከራ፣እስራትና ግድያ የትየለሌ ነው።

ራሱን ዴሞክራቲክ አድርጐ በማቅረብ ውሎበት በማያውቀው የፖለቲካ ፈለግ ራሱን ዲሞክራት በማስመሰልና ለማቅረብ ብዙ ለፍፏል። አልፎ ተርፎም መልካም አስተዳደርን ይወሸክታል።ሆኖም የወያኔ እውነተኛ ተፈጥሮ እየተጋለጠ መጥቷል። ወያኔ/ኢህአድግ ዛሬ በአገዛዝ ባለቤትነቱ፣ በነፍጥ አንጋችነቱ በተለይም በቅጥረኝነቱ የተነሳ ያደረገው ሁሉ ማለፊያ፣ የተናገረ እውነት ተደርጐ በባእድኑ ዘንድ ቅቡልነት አለው።ይሁን እንጂ ኢትዮጵያዊው በታሪኩ የሚኮራ ሁሉ፣ የወያኔን አገር ጠልለቱንና እያደረሰ ያለውን ጥፋት ተረድቶታል።ወያኔ በባእድኑ ድጋፍ ማግኘቱ በብርቱ የተስተዋለ ነው።የውጩ ኢ_ ሰብዓዊነትና ፀረ_ ኢትዮጵያ የሚጠበቅና የሚፈልጉት ቢሆንም በአገራችን ፋሽዝም ሥር ሰዶ ተስፋፍቷል።

የተፈለገውን ቀለም መሆን የማይታክተውና የማይቸግረው ወያኔ/ህወሃት ደርግ ተገርስሶ በተከፈተው የሥልጣን በር መሰስ ብሎ ከገባ ጀምሮ የአገሪቱ መደፈርና የሕዝብ መዋረድ፣ ስቃይና ሰቆቃ፣መከራና ችግር፣ መሰደድና መገደል፣በጠላት እጅ መውደቅ፣ የአረብ አገሮች አገልጋይና ተወራጅ መሆን፣ መደብደብና መገደል ዛሬ ምንም የማያውቅ ትንሽ ልጅ አንገቱ በጨንቆራ ተቆርጦ መጣል በወገን ላይ የሚፈጸመው ጥቃት የወያኔ አረመኔያዊ የወረሪ አሰተዳደር 23 ዓመት የጥፋት ተግባርና ውጤት ፣ ኢትዮጵያዊነት መካካትና መዳፈርን እየገፉበት ነው።

ፋሽዝምን እንቃወማለን፣ እናወግዛለን እያለ በጫካ ያናፋ የነበረው ወያኔ ዛሬ በዴሞክራሲ ድባብ ሥር እየተገበረው ያለ አገርና ሕዝብን ማዋረድና መዝረፍ፣ መቀጣጫ እያለ በግፍ ማሰርና መግደል ምን ተብሎ ሊጠራ ነው? የዚህ ንጹህ ልጅ መታረድ ከምን የመጣ ነው ? ወደ ኃላ ተመልሰንና የአሁኑን ሁኔታ ብንመለከት ፤ የበዴኖ፣ አጋሮ፣ የአርባጉጉ፣የጎንደር፣ የኝዋኽ፣የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ታፍነው የተሰወሩት፣ የ97ቱ የሰላማዊ ሰልፍ ግድያና እስራት፣ የማጂ_ጉራ ፈርዳ፣ የቤንሻንጉል ማፈናቀልና ግድያ ምን ሊባል ነው? ? ? ሃውዜን እየተባለ የደረሰና የሚደርሰው የጭፍጨፋና አፈና ተግባር ምን ተብሎ ሊጠራ ነው? ከፋሽስት በምን ይለያል? ወያኔ/ህውሃት ሕዝብን በመናቅ የትም አትደርሱም በማለት በትምክህት በመዛት የተናገሩበት ጊዜ በርካታ ነው። አቶ ሰዬ አብረሃ ጦርነትን መስራት እንችላለን ፣ የአቶ መለስ ዜናዊ ትዕግሥት ገደብ አለው በማለት ያሰፈሩትን ለማስረጃ መጥቀስ በቂ ነው፡(ለመሆኑ ሌላው ሕዝብ ጀግንነት የለውም፣ ትዕግሥቱስ ገደብ ገደብ አያውቅም? ያውም እየተበደለ)ግብዝነት ወይስ ምን?



**እደዚህ እንታረድ ! ወልደን ላናሳድግ ! ትተኪ ትውልድ ላይኖረን ! በፍርሃት ንጹሃን ሲታረዱ ምን እያልን ፣ምን እያሰብን ነው?**

በአገራችንና በሕዝባችን ታሪክ ውስጥ ከቶም እንድ እንደአሁኑ ሳንጃ በአንገቱ ላይ ተወድሮ ጦር ተሰብቆበት የሚገኝ ጊዜ የለም።ፋሽዝም ዛሬ በወያኔ/ህወሃት ጊዜ ነግሷል ሥርም ሰዷል።በሥልጣን ላይ ለመቆት፣ሃብቷን በዝብዞና ሸጦ ለማፈራረስ በታቀደው የአገዛዝ ሸብር ተግባር፣ ፋሽዝም በዴሞክራሲ ታዛ ሥር ወያኔ በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ እየፈጸመው ያለ ለመሆኑ ሁሉም አገር ወዳድና ወዳጅ ሁሉ ይረዳው።

ፋሽስት_ ሕዝብ ይጨፈጭፋል፣ያስፈራራል፤ ፋሽስት_ የማደናገሪያ ፕሮፓጋንዳን ያስፋፋል፣ ውሸት ይዋሻል፤ ፋሽስት_ ትምክህተኛና ጦርነት ፈላጊ ነው።ፋሽስት_ ራስ ወዳዶችን፣ ሆዳሞችን፣ግብዞችን፣ዱርየዎችን መሳሪያ ያደርጋል፤ ፋሽስት ድርጅቶችን ያስፋፋል፣ ተለጣፊ ያበዛል _ _ _ ወዘተ ይላል የፋሽስት ተንታኜው።

ፋሽስቶች መንግሥታቸውን የሚመሰርቱት በብዙሃኑ አንገት ላይ ካራ ወይንም ሳንጃ በመደገን ነው።ይህ ዛሬ በዚህ ልጅ ህይወት ላይ የተፈጸመው ተግባራቸው ነው። ፋሽስቶች ቀይ ሽብር እያሉ የሚጨፈጭፉት ተቃዋሚ ግለሰቦችን ለመግደል ብቻ አይደለም እነሱን በማሰቃየትና በሚያሰቅቅ መልክ በመግደል ሕዝቡ እንዲሸበርና እንዲፈራ በማድረግ ለመግዛት ነው ይላል።ፋሽስት ጭቁኖችን እየጨፈጨፈ በማስፈራራት የሚገዛ ነው ከተባለ ከሕወሓት/ወያኔ በላቀ ያውም በዘሩ/ቋንቋው ምክንያት በታሪካችን ማግኘት ያስቸግራል።ወያኔ በዚህ ሥራው ከፋሽስት በምን ይለያል? እየተፈጸመብን?እየተደረገና እያየነው ፣ እየደረሰብ ነው።ፋሽስታዊ ሥራ በአገርና ሕዝብ በኢትዮጵያ ላይ እየተፈጸመ ነው።

ወያኔ/ህ ሕዝብ እንደ መንጋ ይከተላቸው ዘንድ  እንዳሴሩ ናቸው፣ወዳሴ ከላሰማ የመኖር ዋስትናውን አደጋ ላይ ጥለውታል። ፋሽስት የማደናገሪያ ፕሮፓጋንዳን ያስፋፋል፣ ሁሉም አዲሃሪያን ሕዝቡ አሜን ብሎ እንድገዛ የማያቋርጥ ማደናቆሪያ ውሸትን ይዋሻሉ።ዛሬ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ከሥራ ተባረው የምጽዋት አሳዳጅ በሆኑበት ፣ከትምህርት ቤት ተፈናቅለውና መጠኑ ተወስኖ ፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች፣አባላቶቹ ሲታሰሩ፣ሲገደሉ፣ጽፈት ቤታቸው ሲዘጋ፣ የነፃ ፕረስ ፣ ጽሀፊዎች፣ አሳታሚዎች ዘብጥያ የሚወረወሩበት፣የሃይማኖት ቅራኔና ጣልቃ ገብነት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመከራ፣ የእንግልት፣ የችግር ጩሆት በሚያሰማበትና አገር በምትፈራርስበት በዚህ  ፈታኝ ወቅት ወያኔ በፕሮፓጋንዳ መሳሪያዎቹ ምን እያሰማን ነው? ምን እያወጋን ነው? ሰላም ሰፍኖ፣ የዲሞክራሲ ፀደይ ፈክቶ፣ ፍትህ ሰፍኖ፣ አንድነት ተጠናክሮ፣ ብሔራዊ ብልጽግና ተገኝቶ፣ ልማቱ፣ህዳሴው፣ጤንነቱ፣ ጥጋቡ፣ የርሻው ምርቱ ሳይቀር 12% አድጐ እየተባለ የውሸት ኩየሳ አይደለም የሚከመርልን!

ፋሽስቶች ዋሾዎች ናቸውና ከወያኔ/ህወሃት የበለጠ ዋሾ የት ሊገኝ እንዳውም የናዚው ጀርመን አዶልፍ ሂትለር የእኔ ታሪክ በሚለው መጸሐፉ ትንንሽ ውሸቶች ተለምዶያዊ ስለሆኑ ትልልቅ ውሸቶችን መዋሸት እንደሚያሻ ነው የገለጸው። ዛሬ ወያኔ/ህውሃት በዋናነት በተለይም ሟቹ መለስ ዜናዊና አገዛዙ  እንደሚጠቀሙበት በግልጽ የታወቀ ነው።ፋሽስት ማደናገሪያ የተፈጥሮውና ተግባሩ በውሸት የገነነ እሙን ሆኗል። ስለዚህም ነው ወያኔ አንድ ጊዜ የግራው አልባኒያ አቀንቃኝ በሌላ ጊዜ ደግሞ የነፃ ገበያ ተርቲበኛ እያለ የሚገላበጠው።ወያኔ ዋሾ የሆነውን ተግባሩን ስንረዳ፣ መለያው የሆነውን ውሸት ስናስተውል ለጽ/ቤታችው ዘበኛ የሌላቸውን፣ በእጃቸው ዱላ እንኳን ያልያዙ ግለሰቦችን ጦርነት አወጁብን፣ ሽብር አስነሱብን፣ ቦምብ አፈነዱ፣አመጽ አስነሱ ብን በማለት ራሱ በራሱ ወንጅሎ በውሸት ምስክርና ፍርድ ቤት ያዳመጠበትና የተቀበለበት ሁኔታ ይጤናል።

ፋሽስት ትምክህተኛ ጦርነት ፈላጊ ነው።ፋሽስታዊያን ፀረ_ ጭቁኖች ስለሆኑ የብዙሃኑን ስብዓዊና ዴሞክራሲያዊ ሙብት አያምኑበትም። ፋሽስት ትምክህተኛ ጦርነት ፈላጊ ነው ተብላል።ትምክህተኝነት የሚመነጨው ከማን አህሎኝ እኩይ ስሜት ባህሪ በመሆኑ ማን አህሎኝ ያለ እኔ  እብሪት የሚቀፈቀፈውና የሚጫረ ከወታደራዊና ፖለቲካዊ የበላይነት እንደሆነ ይገለጻል። ስለሆነም ዛሬ የቤተ መንግሥቱ ባለቤት ወያኔ/ሕውሓት የወታደራዊ የበላይነት የፈጠረለት እብሪት ከዚህም የመነጨ ትምክህትነት አለው። ጦረኛነቱም ደግሞ  አማጢና ሽፍታ በነበረበት በጫካ ዘመኑ  ለመሆኑ በውል ይታወቃል። አሁን በሥልጣን ላይ እያለም ጦርነት መፈለጉ፣ የሚያደርስው ኢ_ ሰብዓዊ ድርጊት ያመለክታል።በየጊዜው የሚያደርስው ጭፍጨፋ፣ በመትረየስ መረፍረፍ፣የአዲስ አበባ ተማሪዎች ላይ በየካቲት አደባባይ የደም ጐርፍ ማፍሰስ፣ገዳማትን ማፍረስና መነኮሳትን ማሳደድና መግደል፣ ሕዝብን ከቦታው ማፈናቀልና መግደል ሃብቱን መቀማት _ _ ወዘተ ወያኔ/ህውሃት ወዳጅነት ለማፍራት ሳይሆን ለጦርነት ፍላጐት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ዘወትር ስለ ሃውዜን  ማውራትና መስበክ ሰላማዊ አያደርም፣ ሰላምንም አያመጣም  ? በተለይ ደግሞ ህጻናትን በዚህ ሁኔታ መግደል አረመኔነት የከፋ የሰይጣን ተግባር ነው።

ወያኔ/ኢህአድግ የፖለቲካ ሥራው ተቃዋሚዎችን ወደ ትጥቅ ትግል እየገፋና አመጽን እየጫረ ጦር ይምጣ እያለ የሚያልም አረመኔ ፋሽስት ነው። ስይጣን ቢያረምም ባህታዊ አይሆንም እደሚሉ የአዛውንቱ ቢሂል የወያኔ ልፈፋው ቢጠና ጦርነት ነው።ወያኔ/ህወሃት ጦርነትን እንደ ታላቅ ጥበቡ፣ እንደ ታላቅ እሴቱ በመቁጠር  ሕዝብን በሚፈልገው መንገድና መልክ ለመቅረጽ መውተርተሩ ዴሞክራሲና ስብዓዊ ሙብት የሚባለውን አለማወቁንና አለማመኑን ያስጤናል።ድሮስ ! ወያኔ ጠባብ ጎጠኛ ፋሽስት ነው ምን መልካም ምግባር ይኖረዋል? ከወያኔ/ኢህአድግ ሰላምና ዴሞክራሲ የማይታሰብ ነው።

ፋሽስት በራስ ወዳዶች፣ በዱርዬዎች፣በወሮባላዎች የሚመሰረት ነው። ሥራአጥ ወንዶችንና ሴቶችን የጎዳና ተዳዳሪ በማለት ሰይሞ እንደ ቀንደኛ መሳሪያ ይጠቀምባቸዋል።ወያኔ/ህወሃት በኢትዮጵያ 23 ዓመት ያሳየን ይህንኑ ነው። ከየሁለተኛው ደረጃ ፈርጥጠው ጫካ የገቡ የትግራይ ተወላጆች ፣ ቤተሰብ ለማስተዳደር እንኳን ሙከራ ያላደረጉ ተመክሯቸው ነፍሰ ገዳይ የሆኑ ናቸው። እንድሁም የወያኔ ፋሽስት አጃቢዎች በውጭ አገር በስደት የኖሩ ፣ ከትምህርቱ ትምህርት፣ ከኑሮው ኑሮ የሌላቸው የተወነባበደባቸው በርጥባን የኖሩ  በምንዳ ተታለው በበሉበት መጮህ የለመዱ በጨው እንደተታለለች ፍየል ሆዳቸውን አስቀድመው  ከወያኔ ጋር ወግነው የግንቦት የወያኔ አቢዮተኞች በመሆን  ከአድዋና ሃማሴን ጋር ተቀናጅተው የምንወዳትን ኢትዮጵያን፣ነፃነት አፍቃሪ ሕዝቧን እያፈራረሱ ያሉት።ፋሽስታዊ ባህሪያቸውም የሚንጸባረቀው የተማረውንና የሥራ ልምድ ያካበተውን  አገር ወዳድ በማባረርና በማስወጣት በዱርየነትና በወሮበላነት አብረው ያሉት በመሾምና  መሳሪያም በማድረግ ነው።

ፋሽስት ማህበራትን ያስፋፋሉ ሁሉም በማህበር እንዲደራጅ ያደርጋሉ።ነገር ግን ማህበራቱን በራሳቸው ታማኝ መቆጣጠርን የበለጠ አደርገው ይጠቀሙታል።ስለዚህም ፋሽስት ማህበራት ይቋቋማሉ።እነዚህን ማህበራት የራሳቸው የፍላጐት ማሟያ አድርገ ሲጠቀሙባቸው ይገኛሉ።ዛሬ ምናልባትም በታሪካች የመጀመሪያ የሆነው የድርጅቶች ፍልፈላ በዚህ በወያኔ ዘመን ነው እየተካሄደ ያለው።ወያኔ በአምሳሉ እየፈጠረ አህዴድን ተለጣፊ ለዘረኛ አላማው ጭብል መሚያ አድርጓል፣  የብዙ ዜጐችን ደም አፍሷል። አህድንን አቋቁሞ የአማራ ተወካይ ለማድረግ ብዙ ለፍቷል _ _ወዘተ።የልጠፈጠፈው ተለጣፊ ድርጅት የለም ። ወያኔ ከራሱ ትግራይ ክፍል በቀር ተደራቢ ፈጥሮ ያላወጣበት ቦታ አይታይም።ወያኔ ጠባብ ዘረኛና ፋሽስት ድርጅት ነው።ፋሽዝም የወያኔ አገዛዝ አይነተኛ ባህሪ ነው።የጣሊያን ፋሽስት ዓለማ ዛሬ በቆዳ እንጂ በመሰሉ እየተፈጸመ ይገኛል።ይህም በአገራችን የወያኔ አገዛዝ አይነተኛ ባህሪ ሆኖል ይበልጡንም የወያኔ/ህውሃት ፋሽዝም በረቀቀ መልከ በወያኔ ለመካሄዱ  ምስክሩ ራሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈጸመው መከራ ሁሉ ተቀባይ የሆነው ነው።ወያኔ የራሱን መጥፎ ስምና ባህሪ ለሌሎች በመስጠት ለሚፈጽመው ግፍ ሁሉ ሰበብ በማበጀት፣ ማንነቱን ለመሸሽግ ቢጥርም በዴሞክራሲ ሽፋን ቢለፍፍም ፋሽስትነቱ ያገጠጠ፣ ያፈጠጠ ሆኖል። ያዳኝ ውሻ ፀጉር ባፉ ነውና የወያኔ/ህውሃት ባህሪና የጎጠኛነት ተፈጥሮው ፀሐይ የሞቀው ሃቅ ነው።

የወኔ የማንነት ባህሪና ተግባሩ ሁሉ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ናቸው።ወያኔ ተፈጥሮው ጎጠኝነት፣ ባህሪው ፋሽስታዊ ነው። ይህንም ፀረ_ ኢትዮጵያ፣ ፀረ_ኅብረተሰብ፣ ፀረ_ አንድነት፣ኢ _ ዴሞክራሲዊ፣ ኢ_ ሰብዓዊ አረመኔዊ ተግባሩን  ለ23 ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢትዮጵያዊ ትዕግሥትና አርቆ አስተዋይነት ሲደበደብ፣ ሲባረር፣ሲገደል፣ ሃብት_ ንብረቱ ሲዘረፍ፣ ዳርድንበሩ ሲወሰድ፣ አገሩ ለሁለት ስትከፈል፣የውሃ በር ሲታጣ፣በቋንቋ ልዩነት ሲመደብ፣ሲጣሉህና ደም ሲፋስሱህ፣ ስትሰደድ፣ ልጆችህ ለዘመናዊ ባርነት ከአገር ሲወሰዱና ሲወጡ፣ሲገደሉ፣ የተማረ ወገን ሲገደልና ሲሰደድ፣ አገርህ ለውጭ ባለሃብት ስትሸጥ፣ይህ ሁሉ ሲሆን እስከ አሁን በዝምታ ታግሰሃል። እጅግም ዝምታና ትዕግሥት እንደ አለማወቅና ፍርሃት ስለሚታይ መናቅንና መደፈርን ያስከትላል። በዚህም ሁኔታ ዛሬ ኢትዮጵያ ተደፍራለች፣ ሕዝቧ ተዋርዷል፣ ልጆቿዋ በህጻን እድሜአቸው እታረዱ ነው። የታሪክ ክብሯ ተንቋል።ለብዙ ሺህ አመታት የኛ ቀደምት ትውልዶች አጥንት ደማቸውን በማፍስስ ታፍራና ተፈርታ የኖረች አገር ዛሬ በዚህ ወቅት ትውልድ መካን ሆና ጥቃቱና ጥፋቱ እጅግ ተነባብሯል። ኢትዮጵያዊ ወገኔ ሆይ !ፍርሃት ከአደጋ የመከላከያ ባህሪ እንጂ እየሸሹ ለመጥፋትና ለመሞት አይደለም።ይህ ጭቆናና ጥቃት ሊያበሳጭ፣ሊያናድድህና ሊያስቆጣህ ይገባል።ሰውነህና ለመብትና ለነፃነት መታግልና ለመጭውም ትውልድ ለልጆችህ አገር ማቆየት ይኖርብሃል ልጆችህን ማሳረድ የለብህም።ለዚህም ነው አገር አትሞት ጠባቂ ትውልድ አላትና የተባለው።የኛ ቀደምት አባቶች/እናቶች እኛ ሞተን አገር ትኑር ብለው ለኢትዮጵያ ታላቅ መስዋዕትነት ከፍለዋል። ታሪክ ምስክርነትዋን መዝግባለች።ዛሬም የኢትዮጵያዊያን ወኔና ጀብዱ፣አትንኩኝ ባይነት ይደገም።ወያኔ ኢትዮጵያዊነት የሌለው አረመኔ ፋሽስት ነው።

ስለሆነም ይህ  ወያኔዊ ድርጊትና ባህሪ ከኢትዮጵያ ምድር እንዲወገድና እንዲጠፋ ወያኔ /ህውሃትን ወይንም በሽፋን ስሙ ኢህአድግ በምርጫ ሳይሆን በሕዝባዊ አመጽ ተገፍትሮና ተፈንግሎ ከነርዕዮተ ዓለሙና ሥርዓቱ መወገድ አለበት። በተለጣፊ የፖለቲካና ስውር አጀንዳ ባላቸው ድርጅቶች ሕዝብ ግራ ሳይጋባ የአድነት ወገንን አውቆና ለይተህ ትግሉን በማጧጧፍ ሕዝብ በአንድኑቱና በኢትዮጵያዊነቱ ብርታት ክንዱን አስተባብሮ ለብሔራዊ አለኝታው በፅናት መታገል ይጠበቅበታል። በኢትዮጵያዊነቱ፣ በአህዳዊ ኢትዮጵያ ታሪክ ለሚኮራና በአገር አለኝታ ኃላፊነትና ግደታ ለሚሰማው በተግባርም መስዋዕትነት ለአቀደ ሁሉ የቀረበ ጥሪ ጭምር ነው። ለትዕግሥት ገደብ እንስጥ፣ አንዋረድ ፣ትውልድ እንጠብቅ፣አገርና ሕዝብ እናድን፣ ልጆች አናስገድል!

## ፋሽስት ይደመሰሳል ! !!

## ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !

## ምንጊዜም ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነትና አረንጓዴ_ቢጫ_ ቀይ ሰንዴቅ ዓላማችን !

10/17/2014